# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር

# ብሔራዊ የሥነ-ልክ ኢንስቲትዩት

---

## የህክምና መሳሪያዎች ተከላ፣ኮሚሽኒንግና ጥገና አገልግሎት
## የብቃት ማረጋገጫ መስፈርቶች
## የፈቃድ መስጫ መደብ 63157

---

**ህዳር 2006**

## ማውጫ


| ቁጥር | ርዕስ | ገፅ |
|---|---|---|
| 1 | መግቢያ | 3 |
| 2 | ርዕስ | 3 |
| 3 | ትርጓሜ | 3 |
| 4 | ዓላማ | 5 |
| 5 | የህክምና መሳሪያዎች ተከላ፣ ኮሚሽኒንግና ጥገና የአገልግሎት ወሰን | 5 |
| 6 | የብቃት አጣሪ ኮሚቴ | 6 |
| 7 | የሳይንስ መሳሪያዎች ተከላ ኮሚሽኒንግ ጥገናና ማማከር አገልግሎት ብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥ ሂደት | 6 |
| 7.1 | ማመልከቻ አቀራረብ | 6 |
| 8 | ስለ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አሰጣጥ | 7 |
| 8.1 | የሰነድና የአካል ግምገማ | 7 |
| 8.2 | የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ የሚያገለግልበት የጊዜ ገደብ፣ዕድሳት፣ዕገዳና ስረዛ | 8 |
| 9 | የብቃት ማረጋገጫ መስፈርቶች | 8 |
| 9.1 | የሰው ኃይል | 9 |
| 9.2 | የስራ ቦታ | 9 |
| 9.3 | የመለኪያ፣የፍተሻና የጥገና መሳሪያዎች | 10 |
| 9.4 | የአሰራር ሥርዓት | 11 |
| 10 | ስለ ሙያ ሥነ-ምግባር | 12 |

## 1. መግቢያ

ተጠሪነቱ ለሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የሆነው ብሄራዊ የሥነ-ልክ ኢንስቲትዩት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የሚኒስትሮች ም/ቤት ደንብ ቁጥር 194/2003 አንቀፅ 6 ንዑስ አንቀፅ 16 መሰረት በተሰጠው ሥልጣንና ተግባር እንዲሁም በንግድ ሚ/ር ፍቃድ መስጫ መደብ ቁጥር 63157 መሰረት በህክምና መሳሪያዎች ተከላ፣ ኮሚሽኒንግና ጥገና የንግድ ዘርፍ ለተሰማሩ ወይም ለሚሰማሩ ሁሉ ንዲያገለግል በማሰብ ይህንን የብቃት ማረጋገጫ መስፈርት አዘጋጅቷል።

## 2. ርዕስ

ይህ ሰነድ የህክምና መሳሪያዎች ተከላ፣ ኮሚሽኒንግና ጥገና አገልግሎት የብቃት ማረጋገጫ መስፈርቶች ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## 3. ትርጊሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ሰነድ ውስጥ፦

***"ሰው"*** ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው።

**"የህክምና መሳሪያ"** ማለት ለሰው በቀጥ ከ ካሚ ጋር በመገናኘት ለምርመራ፣ ለህክምና፣ ለክትትልና የሰው አካለትን በጊዚያዊነት ወይም በቋሚነት የሚተኩ መሳሪያዎች ሲሆኑ ከታካሚ የሚወሰዱ ናሙናዎችን በህክምና ላቦራቶሮች ለመመርመር የሚስፈልጉ መሳሪያዎች፣ የስቴሪላይዜሽን፣ የእጥበት፣ የቀዝቃዛ ሰንሰለት መሳሪዎችንና ሌሎች ድጋፍ ሠጪ የሆስፒታል መሳሪያዎችን ይጨምራል። በተመሳሳይ ሁኔታ ለ ንስሳት ህክምና የሚያገለገሉ መሳሪያዎችንም ያካትታል።

**"የህክምና መሣሪያ ተከላ"** የአምራች ድርጅቱ የተከላ መመሪያን በመከተል አንድን የህክምና መሳሪያ የተላያዩ አካሎችን አስፈላጊ ግብዐቶችን በአግባቡ በመጠቀም በጥንቃቄ በመፈተሽና በመገጣጠም፣ የኃይል ፍጆታውን በማወቅ የኤሌክትሪክና

ሌሎች ግብአቶችን በመዘርጋት እንዲሁም እንዳስፈላጊነቱ የአካባቢያዊ ሁኔታዎችንና ሌሎች ቴክኒካዊ መረጃዎችን አቀናጅቶ ለመሳሪያው በማቅረብ ለግልጋሎት ዝግጁ የማድረግ የስራ ሂደት ነው።

**"የህክምና መሣሪያ ኮሚሽኒግ"** ማለት አዲስ የህክምና መሣሪያ ከተተከለ በኋላ ጥቅም ላይ ከመዋሉ በፊት ተከ ይ የሆኑ የሙከራና የማስተካከል ስራ በመስራት መሣሪያው በአምራቹ ድርጅት መስፈርት መሰረት በትክክል ለመስራቱና በተጠቃሚዎችም ሆነ በ ካሚዎች ላይ ጉዳት አለማድረሱ የሚረጋገጥበት የቴክኒክ ስራ ነው። የኮሚሽኒንግ ሥራ ሁል ጊዜም ባይሆንም አብዛኛውን ጊዜ ቋሚና ከፍተኛ የቴክኖሎጂ ውስብስብነት ያላቸው አዳዲስ መሣሪያዎች ከተተከሉ በኋላ በመቀጠል የሚከናወን ተግባር ነው።

**"የህክምና መሳሪያ ጥገና"** ማለት አንድ የህክምና መሳሪያ ኮሚሽን ተደርጎ ሥራ ላይ ከዋለበት ጊዜ ጀምሮ በቴክኒክ ባለሙያ ና በተጠቃሚዎች እስከ ህይወት ዘመን ፍፃሜው ድረስ የሚደረግለት ንክብካቤ፣ የቅድመ ብልሽት ጥገና ና ተበላሽቶ በአምራች ድርጅቱ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች በማስተካከል ወዲያው ወደነበረበት ሁኔታ በመመለስ ስራ ላይ የማዋል (የብልሽት ጥገና) ተግባራትን ያካትትታል ።

- የብልሽት ጥገና ማለት የተበላሸውን የመሣሪያው ክፍል በመለየት፣ በመቀየርና በአምራች ድርጅቱ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች በማስተካከል ወደ ነበረበት ትክክለኛ አሰራሩ መመለስ ነው።
- የቅድመ ብልሽት(የ ቀደ) ጥገና ማለት በአምራች ድርጅቱ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ተከትሎ በየወቅቱ መከናወን የሚገባቸውን የፍተሻና የማስተካከል ፕሮሲጀሮች በቅደም ተከተል በማከናውን አንድ የህክምና መሳሪያ በትክክል የስራ መሆኑ የሚረጋገጥበትና ሊከሰቱ የሚችሉ አሉ ዊ ተፅዕኖዎችንና ብልሽቶችን በመቀነስ የመሣሪያው ደህንነት በቴክኒክ ምርመራ የሚረጋገጥበት ተግባር ነው።

**"ኢንስቲትዩት"** ማለት የኢትዮጵያ ብሄራዊ ሥነ-ልክ ኢንስቲትዩት ነው።

**”የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት”** ማለት የሳይንስ መሳሪያዎች ተከላ፣ ኮሚሽኒንግና፣ ጥገና አገልግሎቶችን ለሚሰጥ ድርጅት በኢትዮጵያ ብሔራዊ ሥነ-ልክ ኢንስቲትዩት የሚሰጥ የብቃት የምስክር ወረቀት ነው፡፡

**“አመልካች”** ማለት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እንዲሰጠው ማመልከቻ ያቀረበ ሰው ነው ፡፡

**“ሚኒስቴር”** ማለት የኢትዮጵያ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ነው፡፡

**4. ዓላማ**

ብሄራዊ የሥነ-ልክ ኢንስቲትዩት በንግድ ፍቃድ መስጫ መደብ ቁጥር 63157" የህክምና መሳሪያዎች ተከላ፣ ኮሚሽኒንግና፣ ጥገና" ዋና የንግድ ዘርፍ ግልፅ መስፈርቶችን በማዘጋጀትና መሟላ ቸውንም በሰነድና በአካል ግምገማ በማረጋገጥ በዘርፉ ለተሰማሩ ወይም ለመሰማራት ላሰቡ አመልካቾች የብቃት ማረጋገጫ መስጠት ነው፡፡

**5. የህክምና መሳሪያዎች ተከላ፣ ኮሚሽኒንግና ጥገና አገልግሎት ወሰን**

5.1 የህክምና መሳሪያዎች ተከላ፣ ኮሚሽኒንግና ጥገና አገልግሎት ላይ መስጠት የሚያስችል የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚፈልግ አመልካች ከላይ ለህክምና መሳሪያዎች በተቀመጠው ትርጓሜና በአመላካች የህክምና መሳሪያዎች ዝርዝር የተካተቱትን (አባሪ 2ትንና አባሪ 3ትን) በማጤን ይሆናል፡፡ ፡፡

5.2 የህክምና መሳሪያዎች ተከላ፣ ኮሚሽኒንግና ጥገና አገልግሎት የህክምና መሳሪያዎችን የተክኖሎጂ ውስብስብነት ደረጃና የባለሙያዎችን የትምህርት ዝግጅትና የስራ ልምድ ተከትሎ በሁለት ደረጃዎች ተከፍሎ የሚከናወን ይሆናል፡፡

- ደረጃ አንድ በድጋፍ ሠጪ የህክምና መሳሪያዎች ተከላ፣ ኮሚሽኒንግና ጥገና አገልግሎት ላይ የሚሰጥ ሲሆን
- ደረጃ ሁለት ደግሞ ከፍተኛ የቴክኖሎጂ ውሰብሰብነት ያላቸውን የምስል፣ ትንተና፣ የማከሚያና የክትትል መሳሪያዎች ተከላ፣ ኮሚሽኒንግና ጥገና አገልግሎት ሲሆን በደረጃ አንድ የተዘረዘሩትን መሳሪያዎችንም የሚያከትት ይሆናል፡፡

5.3 ይህ የብቃት ማረጋገጫ በሳይንስና ኑክሊር መሳሪያዎች ተከላ፣ ኮሚሽኒንግና ጥገና አገልግሎት ላይ ተፈፃሚ አይሆንም::

## 6. የብቃት አጣሪ ኮሚቴ

6.1 የብቃት አጣሪ ኮሚቴው በኢንስቲትዩቱ በብሔራዊ የሥነ-ልክ ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር የሚሰየሙ አምስት አባላት ይኖሩ ል::
6.2 ኮሚቴው ቢያንስ በሳምንት አንድ ቀን ንዳስፈላጊነቱ ይሰበሰባል
6.3 ኮሚቴው የብቃት ምሥክር ወረቀት አሠጣጥን አስመልክቶ ለቀረበ ማመልከቻን ይገመግማል: ለዋና ዳሬክተሩ የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል::
6.4 በቀረበው የውሳኔ ሀሳብ መሰረት የኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር ውሳኔ ይሰጣል::
6.5 አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ይህንን መስፈርት ንዲሻሻል ለበላይ ላፊ የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል::

## 7. የህክምና መሳሪያዎች ተከላ፣ ኮሚሽኒንግና ጥገና አገልግሎት የብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥ ሂደት

### 7.1 ማመልከቻ አቀራረብ

የህክምና መሳሪያዎች ተከላ፣ ኮሚሽኒንግና ጥገና አገልግሎት ለመስጠት ተቋማዊ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ማግኘት የሚፈልግ ማንኛውም አመልካች:-

7.1.1 በንግድ ሚ/ር ወይም ከሚመለከተው የክልል ንግድ ቢሮ የንገድ ምዝገባ መግለጫ ከማመልከቻው ጋር አያይዞ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

7.1.2 የህክምና መሳሪያዎች ተከላ፣ ኮሚሽኒንግና ጥገና አገልግሎት ለመስጠት የብቃት ማረጋገጫ የሚፈልግ ማንኛውም የንግድ ድርጅት ባለቤት የቴክኒክ ሙያውን በዕውቀት ለመምራት ተፈላጊውን የትምህርት ዝግጅትና ቀጥተኛ የስራ ልምድ ማሟላት ይጠበቅበታል፡፡

7.1.3 ከላይ በ7.1.2 የተገፀው ተሟልቶ በማይገኝበት ጊዜ ድርጅቱ የቴክኒክ ሙያውን በዕውቀት ለመመራት ተፈላጊውን የትምህርትና ዝግጅትና ቀጥተኛልምድ የሚያሟላ ቀጥሮ ሊያሰራ ይችላል፡፡

7.1.4 የቴክኒክ አገልግሎቱን የሚመራው ባለሙያ አሰመልክቶ

- ሲቪ

- የትምህርት ማስረጃ ኮፒ
- በኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድ ኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን በሙያው የተሰጠ የምዝገባና ላይሰንስ ምስክር ወረቀት ኮፒ (ከዋናው ጋር የሚመሳከር)
- በመስኩ ቀጥተኛ የሆነ የስራ ልምድ ኮፒ (ከዋናው ጋር የሚመሳከር)
- የተፈፀመ የስራ ሥምምነት ውል (አመልካች ድርጅት የቴክኒክ ስራውን የሚመራ ባለሙያ ቀጥሮ የሚያሰራ ከሆነ)

7.1.5 የአመልካች ሙሉ አድራሻ (ስልክ፣ኢሜል ወዘተ ይጨምራል) አና ሌሎች ተፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን በማከል ለዚሁ የተዘጋጀውን ፎርም (አባሪ 1) ሞልቶ ለኢንስቲትዩቱ ያቀርባል::

# 8. ስለ ብቃት ምስክር ወረቀት አሰጣጥ

## 8.1. የሰነድና የአካል ግምገማ

### 8.1.1 የሰነድ ግምገማ

አመልካች በማመልከቻው ያቀረባቸው ሰነዶች አግባብነት ከዋናው ሰነድ ጋር የተመሳከረ በአባሪ 4 በተመለከተው ቼክሊስት መሰረት ይገመገማል:: የህንን ያሟላ አመልካች ለአካል ግምገማ ያልፋል ከላላፈ ግን እንዲያውቀው በደብዳቤ ይገለፅለ ል::

### 8.1.2 የአካል ግምገማ

አመልካች የሠነድ ግምገማውን አሟልቶ ሲገኝ በስራ ቦ ው በተቀጠረበት ቀን በመገኘት በአባሪ 5 በተመለከተው ቼክሊስት መሰረት ይገመገማል:: ካላላፈ ግን እንዲያውቀው በደብዳቤ ይገለፅለ ል፤ ንዲያሟላም የጊዜ ገደብ ይሰጠዋል::

8.1.3 የተደረገው የሠነድና የአካል ግምገማ ሪፖርት ከውሳኔ ሃሳብ ጋር ለዋና ዳይሬክተር ይቀርባል::

8.1.4 ዋና ዳይሬክተሩ ውሳኔ ከሰጠበት ቀን ጀምሮ በአምስት ቀናት ውሰጥ የብቃት ምስክር ወረቀቱ ለአመልካቹ ይሰጠዋል::

8.1.5 የብቃት ምስክር ወረቀቱ የሚሰጠው ለደርጅቱ ሆኖ የቴክኒክ አገልግሎቱን በሚመራው ባለሙያ ስም ይሆናል፡፡

## 8.2 የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ የሚያገለግልበት የጊዜ ወሰን፣ ዕድሳት፣ዕገዳና ስረዛ

8.3.1 የቴክኒክ ሙያውን የሚመራው ባለሙያ ሲለቅ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ በተተኪ ባለሙያ ንደገና ቀረበ መ የት ይኖርበ ል፡፡

8.3.2 የቴክኒክ አገልግሎት ሰጪው የብቃት የምስክር ወረቀት ያገኘበትን ተፈላጊ ሁኔ ዎች ምንጊዜም አሟልቶ መገኘት አለበት፡፡

8.3.3 የብቃት መስክር ወረቀቱ የሚያገለግለው ለአንድ የበጀት ዓመት ብቻ ይሆናል፡፡ የዕድሳት ጊዜ በዓመቱ ከሐምሌ ወር ስከ ህሳስ ይሆናል፡፡ ሆኖም በቅድሚያ ከንግድ ሚ/ር ወይም ከሚመለከተው የክልል ቢሮ የተሰጠ የማደሻ ማስ ወሻ መቅረብ ይኖርበ ል፡፡

8.3.4 በብቃት የምስክር ወረቀቱ ከተሰጠበት ወሰን ውጭ አገልግሎት መስጠት አይቻልም፡፡

8.3.5 የሙያ ምስክር ወረቀት ንደጠፋ ወይም አንደተበላሸ ተጠቅሶ በማመልከቻ ከቀረበ በኢኒስቲትዩቱ የተጣለውን የብር ቅጣት በድጋሚ ሊሰጥ ይችላል

8.3.6 ድርጅቱ ስራውን በራሱ ወይም በሌላ ህጋዊ በሆነ ምክንያት ሲያቋርጥ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱ ሊሰረዝ ይችላል፡፡

8.3.7 ከላይ በ"**8.3.1** ስከ **8.3.4**" የተመለከቱት ተሟልተው ባልተገኙበት ሁኔ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱ ሊ ገድ ይችላል፡፡

# 9. የብቃት ማረጋገጫ መስፈርቶች

## 9.1 የስው ኃይል

9.1.1 አመልካች የህክምና መሳሪያዎች ተከላ፣ ኮሚሽኒንግና ጥገና ላይ የትምህርት ዝግጅ ቸው የሚፈቅድላቸውና ልምድ ያላቸውን ባለሙያዎች ሊያሰማራ ይችላል፡፡

9.1.2 ከላይ የተመለከተው አንቀፅ ንደተጠበቀ ሆኖ አመልካቹ ንዳቀረበው የህክምና መሳሪያዎች ተከላ፣ ኮሚሽኒንግና ጥገና አገልግሎት ሰጪነት ወሰን ከዚህ በ ች

በተዘረዘረው መስፈርት መሰረት የቴክኒክ ስራውን የሚመራለት በላሙያ ይመድባል::

- **ከፍተኛ መሀንዲስ (ለደረጃ 2)**

**የትምህርት ዝግጅትና የሙያ ልምድ**

በባዮሜዲካል፣ በኤሌክትሮኒክስ ወይም በኤሌክትሪካል ወይም በሜካኒካል የመጀመሪያ ዲግሪናና በላይ ያለው ሆኖ በኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድ ኒትና ጤና ክብካቤ አሰተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን ቢያነስ በህክምና መሳሪያዎች ጥገና መሀንዲስነት የተመዘገበና ላይሰንስ ያለው:: በሙያው በማገልገል ላይ የሚገኝ ወይም ለአንድ አመት ላልበለጠ ጊዜ ከስራ ያልተለየ

- **ከፍተኛ ቴክኒሻን (ለደረጃ 1)**

**የትምህርት ዝግጅትና የሙያ ልምድ**

በባዮሜዲካል፣ ኤሌክትሮኒክስ ወይም በኤሌክትሪካል ወይም በሜካኒካል የቴክኒክና ሙያ በደረጃ 4 ወይም 5 ተመርቆ በኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድ ኒትና ጤና ክብካቤ አሰተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን በህክምና መሳሪያዎች ጥገና ቴክኒሻንነት የተመዘገበና ላይሰንስ ያለው:: በሙያው በማገልገል ላይ የሚገኝ ወይም ለአንድ አመት ላልበለጠ ከስራ ያልተለየ::

**9.2 የስራ ቦታ**

የህክምና መሳሪዎች ተከላ፣ ኮሚሽኒንግና ጥገና አገልግሎት ለመስጠት የሚስፈልገው የስራ ቦ   የሚከተሉትን አጠቃላይና ልዩ ሁኔ  ዎች ማሟላት ይገባቸዋል::

**9.2.1** የህክምና ኤሌክትሮኒክስና ተጓዳኝ ጥገና ወርክሾፕ ቢያነስ 16 ስኩየር ሜትር ሆኖ የ ላፊ ቢሮን፣ ለጥገና የሚመጡና ተጠግነው ለሚመለሱ መሳሪያዎች ማቆያ፣ ለጥገና ሥራ የሚውሉ መሰሪያዎችን፣ መለዋወጫና ሌሎች ግብአቶችን ማስቀመጫ ክፍሎችን ይጨምራል:: ሆኖም ከኃላፊው በተጨማሪ ባለው የሰው ሃይል  ቁጥር በ4 ስኩየር ሜትር በቴክኒሻን ወይም ኢንጅነር ምጣኔ  ያደገ ይሄዳል::

**9.2.2** ከላይ በ9.2.1 የተመለከተው  ንደተጠበቀ ሆኖ የሜካኒካል ስራዎች የሚካተቱ ከሆነ ከ12- 40 ሜትር ስኩየር የሆነ ራሱን የቻለ ወርክሾፕ የስፈልጋል::

9.2.3 ወርክሾፖቹ የአገራችንን የኤሌክትሪክ መስመር ዝረጋ መስፈርቶችን ባሟላ ሁኔ የተሰራ ሆኖ በተለይ የግራውንዲንግ መስመር ና ለመብራትና ለሶኬቶች ተለይተው የተዘጋጁ ሰርኪዩት ብሬከሮች በጥንቃቄ መዘርጋት አለባቸው::

9.2.4 ወርክሾፖቹ ከ25 ዲግሪ ሴንቲግሬድ ውስጣዊ ሙቀት በላይ እንዳይሁኑና ከተለያዩ አቧራማ ርጥበት አዘል ሁኔ ዎች የተጠበቁ መሆን አለባቸው::

9.2.5 የሥራ ላይ ደህንነት መጠበቂያዎች መጀመሪያ ህክምና የ ሳት አደጋ ማጥፊዎች ለአጠቃቀም አመቺ በሆኑ ቦ ዎችና ሀኔ ዎች ተሟልተው መገኘት አለባቸው::

9.2.6 ከሚሰጠው የጥገና አገልግሎት አንፃር በመንግስት የተደነገጉ አግባብነት ያላቸው የስራ ላይ ደህንነት ደንቦችና ደረጃዎች መፈፀም አለባቸው

9.2.7 ለቴክኒካል መፅሐፎች፣ ማኑዋሎች ካ ሎጎችንና የመሳሰሉትን ሰነዶች ለማከማቻና ማንበቢያ ሌሎች ድጋፍ ሰጪ ተግባራትን ለማከናወን የሚያስፈልግ ቢያንስ 9-12 ሜትር ስኩየር ክፍል ንዳስፈላጊነቱ ሊ ይ ይችላል::

9.2.8 መፀዳጃና መ ጠቢያ እንዲሁም የልብስ መቀየሪያ ክፍሎች እንደ ወርክሾፑ ስፋትና ንደ ተግባራቱ ዓይነት ከ 4-12 ሜትር ስኩየር የሚሆን ክፍል ያስፈልጋል::

## 9.3 የመለኪያ፣ የፍተሻና የጥገና መሳሪያዎች

9.3.1 በአመልካቹ በቀረበው የጥገና አገልግሎት ወሰን መሰረት በአንቀፅ 4 ሥር ለተመለከቱት ደረጃዎች አስፈላጊና መሰረ ዊ የሆኑ የመለኪያ፣ የፍተሻና የጥገና መሳሪያዎች ዝርዝር በሚከተለው ሰንጠረዥ ተመልክተዋል::

| ምድብ | የመለኪያ የፍተሻ መሳሪዎች | የጥገና መሳሪያዎች |
|---|---|---|
| ደረጃ 1 | • Digital Multimeter (DMM)<br>• Variable DC power supply<br>• Isolation transformer or Variac<br>• Phase tester<br>• Refrigerant leakage tester<br>• External thermometer<br>• Refrigerator maintenance kits (refrigrant filliling station, oxyacetiline weliding machine etc)<br>• Oscilloscope<br>• Digital IC tester (optional) | • Electronic Engineer/ Technician tools bag (includes screw drivers assortment, side cutters, pliers, wriench, knifes, etc.)<br>• soldering iron/ station<br>• Disoldering /pump station<br>• Workbench 180cm X 75cm X 75cm per technician/Eng.<br>• Dust blower, hand held |

| ምድብ | የመለኪያ የፍተሻ መሳሪዎች | የጥገና መሳሪያዎች |
|---|---|---|
| ደረጃ 2 | • Digital Multimeter (DMM)<br>• Clamp meter<br>• Oscilloscope<br>• Signal generator<br>• Refrigerant leakage tester<br>• External thermometer<br>• Variable DC power supply<br>• Isolation transformer or Variac<br>• phase tester<br>• Refrigerator maintenance kits (refrigrant filliling station, oxyacetiline weliding machine etc)<br>• Electrical Safety analyzer | • Electronic Engineer/ Technician tools bag (includes screw drivers assortment, side cutters, pliers, wriench, knifes, etc.)<br>• Soldering iron/ station<br>• Disoldering pump/ station<br>• Workbench 180cm X 75cm X 75cm per technician/Eng.<br>• Dust blower, hand held |

**9.3.2** አገልግሎቱ አነስተኛ የሜካኒካል አካላትና መለዋወጫዎች ስራን የሚያካትት ከሆነ በአባሪ 6 የተዘረዘሩት መሰረ ዊ መሳሪያዎች ተሟልተው መገኘት አለባቸው፡፡

**9.3.3** አገልግሎቱ መካከለኛ የሜካኒካል አካላትና መለዋወጫዎች ስራን የሚያካትት ከሆነ በአባሪ 7 የተዘረዘሩት መሰረ ዊ መሳሪያዎች ተሟልተው መገኘት አለባቸው፡፡

**9.3.4** ለሳይንስ መሳሪያዎች ተከላ ኮሚሽኒንግና ጥገና አገልግሎቶች የሚወሉ የመለኪያና የመፈተሻ መሳሪያዎች ካሊብሬት ተደርገው ሰርቲፊኬት ሊኖራቸው ይገባል፡፡

## 9.4 የአሰራር ሥርዓት

**9.4.1** የህክምና መሳሪያዎች ተከላ፣ኮሚሽኒነግና ጥገና አገልገሎት ከደንበኛው የአገልግሎት ጥያቄ አንሰቶ ምላሽ እስከሚሰጥበት ድረስ ያሉት ሂደቶች ተዘግበውና አስፈላጊ የሆኑ ፎርሞች ተቀርፀው ግልፅ የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት አለበት፡፡

9.4.2 የህክምና መሳሪያዎች ተከላ፣ኮሚሽኒነግና ጥገና አገለግሎት በተዘረጋውና ተዘግቦ በተያዘው የአሰራር ስርዓት መሰረት መፈፀሙን መከታተልና አንዳስፈለጊነቱም ማሻሻል ያስፈልጋል፡፡

## 10. ስለ ሙያ ሥነ-ምግባር

10.1 በተግባራቶቻችን በምንወስዳቸው ውሳኔዎች ሁሉ የህብረተሰቡን ጤና ፣ ደህንነትና ጥቅሞች ለማስጠበቅ ኃፊነትን መውሰድ ። ይህንንም ሊያጓድሉ የሚችሉ ጉዳዮች ሲከሰቱ ለሚመለከ ቸው ማሳወቅ

10.2 የጥቀም ግጭት ሊያስከትሉ ከሚችሉ ጉዳዮች መራቅ። ሊከሰቱ የሚችሉ መሆናቸው ሲ. ወቅም ለሚመለከ ቸው ወገኖች ማሳወቅ

10.3 ባለው ወይም በቀረበ መረጃ ላይ ተመስርቶ ክሌሞችን ወይም ግምቶችን ሰርቶ ማቅረብ በማያስፈልግበት ጊዜ ተክክለኛና ተአማኒ መሆን

10.4 ቴክኖሎጂን የበለጠ ለማሻሻልና ለመማር እንዲሁም አጠቃቀማቸውንና ሊያስከትሉ የሚችሉትን ጉዳቶች ለማወቅ መጣር

10.5 ቴክኒካዊ ተግባራቶቻችንን ስናከናውን የደረስንበትን የብቃት ደረጃ ሳንለቅ ለመሻሻል ጥረት ማድረግ

10.6 በቴክሊክ አገልግሎቶች አሠጣጥ ሂደት ገንቢ የሆኒ ሂሶችን ለመቀበልና ለማስተካከል መቻል። ሌሎች ለሰጡን ሀሳቦችም በአግባቡ ዕውቅና መስጠት

10.7 የስራ ባልደረቦቻችንንና ሌሎች ወገኖች ፕሮፌሽናል ሙያዎቻቸው እንዲያጎለብቱ መደገፍ እነሱም በተመሳሳይ ይህንን አካሄድ ንዲደግፉ ማገዝ።

10.9 የሌሎችን አ ምሯዊና ቁሳዊ ንበረቶችን እንደራስ መጠበቅ፤ ክብራቸውን መጠበቅ ውነትነት በሌለው መንገድ ጥቅም ለማግኘት አለመሞከር